DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# ኮሮና ቫይረስ 2019 (COVID-19)፣ የመካከለኛ እንክብካቤ ተቋማት(ICF)የቤት ውስጥ ጉብኝት መስፈርቶች

ይህ ሰነድ በደረጃ ሁለት ወቅት በኮሎምቢያ ግዛት ውስጥ የመካከለኛ እንክብካቤ ተቋማት (intermediate care facilities, ICF) የቤት ውስጥ ጉብኝት መስፈርቶችን ይሰጣል። የቤት ውስጥ ጉብኝቶች ሲደረጉ የCOVID-19 የተጋላጭነት አደጋን ለመቀነስ የሚከተሉት እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። በከንቲባ ትእዛዝ 2020-063 ላይ በተደነገገው መሠረት የጉብኝት ገደቦች ለተንከባካቢዎች ወይም አስፈላጊ ጎብኚዎች ወይም ባለሚሎች ተፈጻሚ አይደለም።

## የቤት ውስጥ ጉብኝት መጠየቅ የሚቻልበት መስፈርቶች

- በተቻለ መጠን ከቤት ውስጥ ጉብኝት ይልቅ የውጭ ጉብኝት ተመራጭ ነው።
- በICF ውስጥ የነበሩ ማንኛውም ሰው (ለምሳሌ፣ በተቋሙ ውስጥ የሚኖር ሰው፣ ቀጥተኛ የእንክባካቤ ሰራተኛ፣ ጎብኚ) ውስጥ ቢያንስ ለሁለት ተከታታይ ሳምንታት ምንም አዲስ የCOVID-19 ጉዳዮች መኖር የለበትም።
- በICF ውስጥ በማግለል(ኳረንታይን) ወይም በለይቶ መቆየት ውስጥ የሚኖር ማንም ሰው የለም።
- ICF ከወረርሽኝ ጋር በተያያዘ ምርመራ እያደረገ መሆን የለበትም።
- ተቋማት ያለአንዳች ጥገኝነት ወይም በህዝብ ጤና ክምችት ላይ ጥገኛ ሳይሆኑ ለወረርሽኙ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የሁሉም የግል መጠበቂያ መሳሪያ (personal protective equipment, PPE)የ14 ቀን አቅርቦት ሊኖራቸው ይገባል።

## የቤት ውስጥ ጉብኝት ከመጠየቅዎ በፊት

- ለኗሪ ቤተሰቦች በICF ውስጥ የቤት ውስጥ ጉብኝት እየተከናወነ መሆኑን ያሳውቋቸው። ማስታወቂያው የሚከተለውን ማካተት አለበት፣
  - በICF የሚኖሩ ሰዎች ደህንነትን ለመጠበቅ የተወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች።
  - በጉብኝት የሚጠበቁ ነገሮች እና መስፈርቶች። ማስታወቂያው ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፣
    - የምልክት ማጣሪያ ሂደት መግለጫ።
    - የጭምብል እና የማህበራዊ ርቀት መስፈርቶች፣ አስፈላጊ ሲሆን ሰራተኛን እንዴት መጥራት እንደሚቻል፣ እና ጎብኚ እንዳይገባ የሚከለከልበት ምክንያትን ጨምሮ የቤት ውስጥ እና የውጭ ጉብኝቶች ሁሉም የስምምነት ግዴታዎች።
    - ጎብኚዎች ከጉብኝታቸው በፊት፣ ሲደርሱ፣ እና በጉብኝት ወቅት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች።

## የቤት ውስጥ ጉብኘት ሲጀምር

- የቤት ውስጥ ጉብኝትን የጭምብል እና የማህበራዊ ርቀት መስፈርቶቹን ለሚያከብሩ ጎብኚዎች ብቻ ይፍቀዱ።
- በICF ለሚኖር ሰው በአንድ የጉብኝት ጊዜ አንድ ጎብኚ ብቻ ይፈቀዳል።
- ለቤት ውስጥ ጉብኝት በሚያገለግለው ቦታ የግለሰቦች መሰብሰብ አለመኖሩን ማረጋገጥ።
- ICF ደህንነት በተጠበቀ ሁኔታ ሰዎችን እንዲያስተናግድ እና የጥንቃቄ እርምጃዎች መተግበራቸውን ለመቆጣጠር በቂ ሰራተኞች እንዲኖረው ለማስቻል ጎብኚዎች አስቀድመው ለጉብኝት ቀጠሮ እንዲያስይዙ ይጠይቁ።
- ተቋማት ጎብኚዎች ወይም ህክምና ነክ ያልሆነ አገልግሎት የሚሰጡ አገልግሎት አቅራቢዎች ወደ ICF ከመግባታቸው በፊት ምርመራ ማከናወን አለባቸው። ተቋማት የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፣
  - ሁሉንም ጎብኚዎች እና አገልግሎት አቅራቢዎች መመርመር።
    - የሙቀት ምርመራ እና የምልክት ማጣሪያን ማከናወን።
    - ጎብኚዎች ከትኩሳት ነጻ፣ ከምልክቶች ነጻ፣ እና ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ COVID-19 ላለበት ሰው ተጋላጭ ያልነበሩ መሆን አለባቸው።
    - ጎብኚዎች በ[coronavirus.dc.gov/phasetwo](coronavirus.dc.gov/phasetwo)ላይ በተገለጸው መሰረት ከፍተኛ ስጋት ወዳለው ክልል ፣ ወይም በDC Health የጉዞ መመሪያ ላይ በተገለጸው መሠረት ወደ ደረጃ 3(ከፍተኛ ስጋት)ሀገር በተደረገ አስገዳጅ ባልሆነ ጉዞ ምክንያት በማግለል(ኳረንቲን)ላይ መሆን የለባቸውም።
    - ለማጣሪያ መሳሪያ መምሪያ፣ይጎብኙ [coronavirus.dc.gov/healthguidance](coronavirus.dc.gov/healthguidance).
  - ጎብኚው የትንፋሽ ማስወጫ የሌለው የፊት ጭምብል ወይም የጨርቅ መሸፈኛ ማድረጋቸውን፣እና ጭምብሉ የጎብኚውን አፍንጫ እና አፍ መሸፈኑን ያረጋግጡ።
  - ጎብኚው ወደ ICF ሲገቡ እና ሲወጡ የእጅ ንጽህና እንዲያከናውኑ ያድርጉ።
- የጎብኚዎቹን ሙሉ ስም እና የሚገኙበት አድራሻን መዝግበው ይያዙ፣እና ይህን ሪከርድ ንኪኪን ለመለየት እንዲረዳ ለ30 ቀናት ያያዙት።
- ምርመራው ያላለፉ ወይም ማናቸውንም መስፈርቶች ለማክበር ፍቃደኛ ያልሆኑ ጎብኚዎችን ወይም አገልግሎት አቅራቢዎችን እንዳይገቡ ይከልክሉ።

## በቤት ውስጥ ጉብኙት ወቅት

- ነብኚዎች በጉብኙቱ ወቅት በሙሉ የጨርቅ የፊት መሸፈኛ ወይም ጭምብል ማድረግ እና በICF ውስጥ ከሚኖረው ሰው የ6 ጫማ ርቀት መጠበቅ አለባቸው።
- ነብኚዎች ጉብኙቱ እንዲካሄድ የተመደበበት ስፍራ ላይ ብቻ መወሰን አለባቸው።
- ነብኚዎች ሊነበኙት ያቀዱትን ኗሪ ብቻ በተመደበው የጉብኙት ስፍራ መነብኘት አለባቸው።
- በICF ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በጉብኙቱ ወቅት በሁሉም ጊዜያት የጨርቅ የፊት መሸፈኛዎችን ማድረግ አለባቸው። የጨርቅ የፊት መሸፈኛዎች ራሳቸውን በሳቱ፣ችሎታ ባጡ፣ወይም በማንኛውም መልኩ ያለእርዳታ ጭምብሉን ማውለቅ በማይችሉ ማንኛውም ሰው ላይ ማድረግ አይቻልም።
- የቤት ውስጥ ጉብኙትን ተገቢ ማህበራዊ ርቀትን የሚፈቅዱ ቦታዎች ላይ ይገድቡ።
    - ቦታው ተገቢ የአየር ዝውውር (ክፍት መስኮቶች፣ ወዘተ) ሊኖሩት ይገባል።
    - የጉብኙት ስፍራው በአንድ ጉብኙት ወቅት ለአንድ ኗሪ እና ነብኚያቸው አገልግሎት ብቻ መዋል አለበት።
    - ጉብኙቶች ለ1 ሰዓት ብቻ መገደብ አለበት።
    - ጉብኙቶቹ እስኪጠናቀቀኡ እና ቦታው ተጸድቶ ዲስኢንፌክት እስኪደረግ ድረስ ማንኛውም ኗሪ ወደ ቦታው እንዲመጣ ሊፈቀድለት አይገባም።
    - ጉብኙቱ የተካሄደው በግለሰቡ ክፍል ውስጥ ከሆነ፣ በጉብኙቱ ወቅት በክፍሉ ውስጥ አብረው የሚኖሩ ሰዎች መኖር የለባቸውም።
- ጭምብል ማውለቅን የሚጠይቁ ተግባራት፣ እንደ መብላት ወይም መጠጣት አይፈቀዱም።

## ከቤት ውስጥ ጉብኙት በኋላ

- ጉብኙቱ ከተጠናቀቀ በኋላ እና ጉብኙቱ ወደተደረገበት ቦታ በክፍሉ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች እንዲገቡ ከማድረግ በፊት ክፍሉ መጸዳት እና ዲስኢንፌክት መደረግ አለበት።
- ICF በከፍተኛ ሁኔታ የሚነኩ ስፍራዎችን (ለምሳሌ፣ማብሪያ እና ማጥፊያዎች፣የኤሊቬተር ቁልፎች፣የበር እጀታዎች) በፈረቃ ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ ማጽዳት እና ዲስኢንፌክት ማድረግ አለበት።

## የCOVID-19 ተጋላጭነት ማስታወቂያ

- ነብኚዎች ከጉብኙቱ ቀን አንስቶ በ14 ቀናት ውስጥ ምልክቶችን ካሳዩ ወይም ለCOVID-19 ተመርምረው ፖዘቲቭ ቢሆኑ ለICF ማሳወቅ አለባቸው።
- የICF ሰራተኞች በICF ውስጥ ጉብኙቱ በተደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ወረርሽኝ ከተከሰተ፣ለነብኚዎች ማሳወቅ እና ነብኙው(ዎቹ)እንዲመረመሩ መምከር አለባቸው።

## ማግለያዎች

- የፊት መሸፈኛ፣የማህበራዊ ርቀት፣እና ሌሎች የተቋም መስፈርቶችን ማክበር የማይችሉ ነብኚዎች የቤት ውስጥ እና የውጭ ጉብኙቶች ላይ መሳተፍ የለባቸውም።

ወረርሽኙ ሲቀያየር ከዚህ በላይ ያሉት መመሪያዎች መሻሻላቸውን ይቀጥላሉ። እባክዎ በጣም ለቅርብ ጊዜ መረጃ coronavirus.dc.gov ይነብኙ።